# የገጀራው መንግስት

እራሱን ዝቅ አርጎ ፣ የሚያይ በሽተኛ
አቻ ያልተገኘለት ፣ የሃገር ወንጀለኛ
ጥላቻ ተብትቦ ፣ የያዘው እስረኛ
ጃዋር የተባለ ፣ ፅንፈኛ ጎጠኛ
ስራ ፈት ፣ ቦዘኔ ፣ ቄሮ እያደራጀ
አገር ያሸበረ ፣ ህዝብን እያፋጀ
መንግስት ፣ አጋር ሆኖት ፣ እያለን አበጀ
የተጠያቂነት ፣ ስልትን ባቀናጀ
እስከንድር ሊከሰስ ፣ ዛሬ ፣ አዋጅ ታወጀ ።

ጦርነት አወዳሽ ፣ ሰላምን ነቃፊ
የአብሮነት ጠላት ፣ ልዩነት ደጋፊ
ፍቅርን እየገፉ ፣ ፅብን አነፍናፊ
ለንቦጭ የሚጥሉ ፣ ሲተቹ አኩራፊ
እስክንድርን ገፍቶ ፣ ጃዋርን አቃፊ
እንዲህ ያለ ፣ መሪ ፣ አንሻም ቀጣፊ ።

በጠባቦች ምናብ ፣ በጠባብ ገፅታ
ካፍንጫ የማይርቅ ፣ በሆነ ዕይታ
በሃሳብ ልዕልና ፣ ተሟግቶ እማይረታ
ሁሌም ተሸናፊ ፣ ሲሆን በጨዋታ
ጊዘውን ጠብቆ ፣ የማታ የማታ
ማንነት ተጋልጦ ፣ ተሸኝታ ይሉኝታ
ዛቻ ማስፈራራት ፣ ተይዟል ድንፋታ ።

የሸገር ልጅ ፣ ዛሬ ፣ መብቱ እየተቀማ
ላላማቸው ስኬት ፣ አርገውት ኢላማ
ከባሌ ፣ አሩሲ ፣ ከወለጋ ፣ ጅማ
አግበስብሶ አምጥቶ ፣ ስግብግብ አሳማ
መታወቂያ ሲያድል ፣ መስሎት ያልተሰማ
አዱ ገነት ፣ ገማች ፣ በታከለ ኡማ
ለዚህ ፣ ሁሉ ትዕይንት ፣ ተንኮሉን ቅመማ
እጃቸው አለበት ፣ ያብይና ለማ
ህልማቸው ነውና ፣ አዲስ እንድትደማ ።

ተሟግቶ የማይረታ ፣ ደካማ ባህሪ
የሌለውን ጠላት ፣ በምናብ ፈጣሪ
ተበደልኩ እያለ ፣ ሁሌ ቀባጣሪ
የወሮበላ አጋር ፣ ስራው አስነዋሪ
የሰላም የፍቅር ፣ የማይገባው ጥሪ
ሁሉም ተመሳሳይ ፣ የላቸው መካሪ
የገጀራው መንግስት ፣ በሜንጫ አስፈራሪ
ከቶ አይገባውም ፣ ሊሆን ፣ አገር መሪ ።

ታዛቢው

March 22, 2019